# ወርሃዊ የአየር ጠባይ
# ግምገማና እና ትንበያ መጽሔት

## ከጃንዋሪ ከ1-31/2023 የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማ እንዲሁም

## ከፌብሪዋሪ 1-28/2023 የሚኖረው የአየር ጠባይ ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ፌብሪዋሪ 2023
አዲስ አበባ

ርዕስ ገፅ


እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 31/2023 የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማ ........................................3

ካርታ 8 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 31/2023 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ ....................4

ካርታ 9 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 31/2023 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት ......................5

ካርታ 10 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 31/2023 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር ........................................6

እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 31/2023 የነበረው የአየር ጠባይ በእርሻ ........................................7

ሥራ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ........................................7

ካርታ 11 ከጃንዋሪ 1 እስከ 31/2023 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ........................................7

እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 31/2023 የነበረው የአየር ጠባይ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ........................................8

ካርታ 11 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 31/20223 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ........................................8

እ.ኤ.አ ከፌብሪዋሪ 1 እስከ 28/2023 የሚኖረው የአየር ........................................9

ጠባይ አዝማሚያ ........................................9

እ.ኤ.አ ከፌብሪዋሪ 1 እስከ 28/2023 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ........................................9

እ.ኤ.አ ከፌብሪዋሪ 1 እስከ 28/2023 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በውሀው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ........................................10


## እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 31/2023 የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማ

ባለፈው የጃንዋሪ ወር የበጋዉ ደረቅ፣ ፀሃያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ አመዝኖባቸዉ ተስተዉሏል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘም የሌሊትና የማለዳዉ ቅዝቃዜ በተለይም በመጀመሪያውና በሁለተኛው አስር ቀናት ላይ አንፃራዊ በሆነ መልኩ የተጠናከረ ሲሆን፤ በአንዳንድ የሀገሪቱ ደጋማ ሥፍራዎች ላይ የቅዝቃዜው መጠን ከ0 ዲግሪ ሴልሽየስ በታች ሆኖ ተመዝግቧል፡፡ ለአብነት ያህል በደብረብርሀን -1.2፣ -0.8፣ በሐሮማያ -1.4፣ -1.2፣ -0.6 -0.2፣ እንዲሁም በመሐል ሜዳ -1.5 እና 0.0 በዲግሪ ሴልሽስ ሆኖ ተመዝግቧል፡፡ ይሁን እንጂ በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ አመዝኖባቸው ተስተውላል፡፡ በሌላ በኩል ለዝናብ መፈጠር መንሰኤ የሆኑት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች አንጻራዊ መጠናከር በማሣየታቸው ከነበራቸው የደመና ሽፋን በተለያዩ የሀገሪቱ ሥፍራዎች ላይ ቀላል ዝናብ ተስተውሎባቸዋል፡፡ በሶስተኛው አስራ አንድ ቀናት ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ አመዝኖ ተስተውሏል። ሆኖም በመጨረሻዎቹ ጥቂት ቀናት በተወሰነ መልኩ ወደ ሀገራችን ይገባ ከነበረው እርጥበት አዘል አየር ጋር ተያይዞ በአንዳንድ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የደመና ሽፋን መጨመር ነበር። ከነበረው የደመና ሽፋን መጨመር ጋር በተያያዘ የሌሊትና የማለዳው ቅዝቃዜ ጋብ ብሎ ተስተውሏል።


በወሩ ውስጥ የዘነበው የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ የቦታ ሽፋን አንጻር ሲገመገም ከ5-72 ሚ.ሜ. መጠን ያለው ዝናብ ከአማራ በዋግህምራ፣ በሰሜንና በመካከለኛው ጎንደር እና በምስራቅና ምዕራብ ጎጃም ጥቂት ቦታዎች፤ በአሶሳ፤ በአብዛኛው ጋምቤላ፤ በደቡብ በምዕራብ ኢትዮጵያ፤ ከደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል የደቡብ ኦሞ፣ የባስኬቶና የጎፋ ዞኖች፤ ከኦሮሚያ በኢሉባቦር፣ በጅማ፣ በቄሌም፣ በሆሮ ጉዱሩና በምዕራብ ወለጋ ዞኖች፣ በምዕራብ ሀረርጌ፣ በአርሲና በምዕራብ አርሲ፣ በጅማ፣ በምዕራብ የሸዋ ዞኖች፣ እንዲሁም በጉጂ ላይ ከ5-72 ሚ.ሜ የሚደርስ ከ2-7 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 8 እና 9) ፡፡

በወሩ ውስጥ የዘነበው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር ሲነፃፀር ከአማራ በዋግህምራ፣ በሰሜንና በመካከለኛው ጎንደር እንዲሁም በምስራቅና ምዕራብ ጎጃም፤ የምዕራብ ሀረርጌና የአርሲ ዞኖች፣ በአሶሳ እንዲሁም በሸካ ዞኖች ላይ መደበኛና ከመደበኛ በላይ የሆነ የዝናብ መጠን የነበራቸዉ ሲሆን፤ የተቀት የሀገሪቱ ክፍሎች ደረቅ ሆነው ሰንብተዋል (ካርታ 10) ፡፡


ካርታ 8   ኢ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 31/2023 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ



ካርታ 9   ኢ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 31/2023 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት



ካርታ 10 ኢ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 31/2023 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር




## እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 31/2023 የነበረው የአየር ጠባይ በእርሻ ሥራ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

በመደበኛ ሁኔታ የጃንዋሪ ወር በአብዛኛው የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ደረቃማ የእርጥበት ሁኔታ የሚያመዝንበት ወቅት ሲሆን፤ በአመዛኙ የድህረ ሰብል ሰብሰባ ተግባራት የሚጠናቀቁበትና ከወሩ አጋማሽ በኃላ በአንዳንድ የበልግ ሰብል አብቃይ አካባቢዎች የማሳ ዝግጅት ተግባራትን ለመጀመር ዝግጅት የሚደረግበት ወቅት ነው።

ባሳለፍነው የጃንዋሪ ወር የነበር የአየር ጠባይ በወቅቱ እየተከናወነ ካለው የግብርና እንቅስቃሴ አንፃር በጎ ጎን ነበረው፡፡ በመሆኑም በወሩ ውስጥ የተስተዋለው ደረቅ የእርጥበት ሁኔታ የደረሱ ሰብሎች እንዲደርቁ፤ በጊዜ እንዲሰበሰቡና የድህረ ሰብል ስብሰባ ተግባራትን ለማከናወን ምቹ ሁኔታ ነበረዉ፡፡ በሌላ መልኩ በአንዳንድ የሰሜን፣ የመካከለኛዉ እና የምስራቅ የሀገሪቱ ደጋማ ስፍራዎች ላይ ከቀኑ ዝቅተኛ የሙቀት መጠን የተነሳ የሌሊትና የማለዳው ቅዝቃዜ ከ0 ዲግሪ ሴልሽየስ በታች ሆኖ ተመዝግቧል፡፡ ይህም የተስተዋለው ቅዝቃዜ በእንሰሳት ጤናና፤ በመስኖ በመታገዝ በሚለሙ የፍራፍሬ ተክሎችና በጓሮ አትክልቶች ላይ በጥቂት ቦታዎች ላይ በተወሰነ መጠን አሉታዊ ጎን ነበረው፡፡ ይሁንና አልፎ አልፎ ባሉት ቀናት ከነበረዉ የደመና ሽፋን በምእራብ አጋማሽ፣ በምስራቅ፣ በሰሜንና በሰሜን መስራቅ  በአንዳንድ ቦታዎች ላይ የተሻለ መጠን ያለዉ እርጥበት ተመዝግቧል፡፡ ይህም ሁኔታ በተለይም ለደረሱና በመሰብሰብ ሂደት ውስጥ ለነበሩ ሰብሎች በጥቂት ቦታዎች አሉታዊ ጎን የነበረው ቢሆንም በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው ለሆኑትም ሆነ ለቋሚ ተክሎች፣ ለአትክልቶችና ለእንስሳት የግጦሽ ሳርና የመጠጥ ውኃ አቅርቦት ላይ የተገኘው እርጥበት ጠቀሜታ ነበረው (ካርታ 11)፡፡


ካርታ 11    ከጃንዋሪ 1 እስከ 31/2023 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



# ኢ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 31/2023 የነበረው የአየር ጠባይ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፍነው የጃንዋሪ 2023 የነበረው የአየር ጠባይ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ የነበረው ገፅታ ከጥቂት በላይኛው ባሮ አኮቦ እና በመካከለኛው ኦሞ ጊቤ መጠነኛ እርጥበት ከመኖሩ በስተቀር በሁሉም ተፋሰሶች ላይ ደረቅና ከፊል ደረቅ ሁኔታ ነበራቸው (ካርታ 11) ፡፡

ካርታ 11 ኢ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 31/20223 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



## እ.ኤ.አ ከፌብሪዋሪ 1 እስከ 28/2023 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ

የፌብሪዋሪ ወር በመደበኛ ሁኔታ የበልግ ዝናብ የሚጀምርበት ጊዜ ነው፡፡ በተለይም ከወሩ አጋማሽ በኋላ ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች እየተጠናከሩ ከመሄዳቸው ጋር ተያይዞ የደቡብ ምዕራብ፣የደቡብ፣የሰሜን ምሥራቅ፣የምሥራቅ፣የመካከለኛውና አጎራባች የስምጥ ሸለቆ ሥፍራዎች የተለያየ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ፡፡

በመጪው ፌብሪዋሪ የበልግ ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ቀስ በቀስ እየተጠናከሩ እንደሚሄዱና ከመደበኛው ጋር የተቀራረበ የዝናብ ሁኔታ ሊኖር እንደሚችል የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ይሁን እንጂ የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት መጠን በአንዳንድን የሰሜን ምዕራብ፣ የምስራቅ፣ የሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ከመደበኛው በላይ እንደሚሆን የትንበያ መረጃችን ያሳያል፡፡

በአጠቃላይ ከኦሮሚያ ክልል <u>የምዕራብ ኦሮሚያ ዞኖች በሆኑት ጅማ፣ኢሉአባቦራ፣ ሰሜን ሸዋ፣ ምዕራብና ምሥራቅ ወለጋ፣ ጥቂት የአርሲ ዞን ሥፍራዎች፣ ምሥራቅና ምዕራብ ሐረርጌ፣!አዲስ አበባ፣ ከደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል በሚገኙት የቤንች ማጂ፣ ጉራጌ፣ ሐዲያ፣ የወላይታ፣የዳውሮ፣ የጋሞ ጎፋ ዞኖች፣ ሰገን ህዝቦች፣ ሲዳማ ክልል፣ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ፣ ከአማራ ክልል የሰሜንና የደቡብ ወሎ ዞኖች፣ ጥቂት የአፋር ዞኖች፣ ከትግራይ ክልል ምሥራቃዊና የደቡባዊ ዞኖች በአብዛኛው ከመደበኛው ጋር የተቀራረበ ዝናብ እንደሚኖራቸው ይጠበቃል፡፡ የተቀሩት የሀገሪቱ ሥፍራዎች ደረቅ ሆነው ይቆያሉ።</u>

## እ.ኤ.አ ከፌብሪዋሪ 1 እስከ 28/2023 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

የፌብሪዋሪ ወር በመደበኛ ሁኔታ የበልግ ወቅት የመጀመሪያ ወር እንደመሆኑ በአብዛኛዎቹ የበልግ ሰብል አምራች በሆኑት አካባቢዎች የእርጥበት ይዘቱ በተለይም ከወሩ አጋማሽ በኋላ ከቀን ወደ ቀን እየተጠናከረ የሚሄድበት ጊዜ ሲሆን ከበልግ ስራ ጋር ተያይዞ በተለያዩ አካባቢዎች የማሳ ዝግጅት በስፋት የሚከናወንበት እና በአንዳንድ አካባቢዎችም አስቀድሞ ዘር መዝራት የሚጀምሩበት ወቅት ነው።

በተሰጠው የአየር ሁኔታ ትንበያ መሰረት በመጪው ፌብሪዋሪ ወር ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ቀስ በቀስ እየተጠናከሩ እንደሚሄዱና ከመደበኛው ጋር የተቀራረበ የዝናብ ሁኔታ ሊኖር እንደሚችል የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ። ይህም የሚጠበቀው እርጥበት ለቋሚ ተክሎችና እና ለተለያዩ የፍራፍሬ ተክሎች የውሃ ፍላጎት መሟላት አዎንታዊ ሚና የሚኖረው ሲሆን በተጨማሪም ሊኖር የሚችለው ዝናብ የአፈር ውስጥ እርጥበትን ከማጎልበት አንጻር አዎንታዊ ሚና የሚኖረው ሲሆን ይህም ሁኔታ በተለይም ከተወሰኑ ቀናት በኋላ የበልግ ወቅት እርሻን አስቀድመው ለሚጀምሩ አካባቢዎች የማሳ ዝግጅትና ዘር ለመዝራት ምቹ ዕድል እንደሚፈጥር ነው። በሌላም በኩል በተቀሩት የሀገሪቱ ክፍሎች የሚጠበቀው ደረቅ ሁኔታ የድህረ ሰብል ስብሰባ እንቅስቃሴ ተግባራትን ላላጠናቀቁ አካባቢዎች አዎንታዊ ሚና ስለሚኖረው አርሶ አደሮች ይህንን ምቹ ሁኔታ በአግባቡ በመጠቀም የድህረ ሰብል ስብሰባ ተግባራትን እንዲያጠናቅቁ ይመከራሉ።

## እ.ኤ.አ ከፌብሪዋሪ 1 እስከ 28/2023 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በውሀው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በመጪው ፌብሪዋሪ ወር እርጥበት ቀስ በቀስ አንፃራዊ በሆነ መልኩ እየተሻሻለ እንደሚሄዱ እና በተለይም በበልግ ተጠቃሚ ተፋሰሶች ላይ መጠነኛ እርጥበት እንደሚኖር የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡ በዚህ መሰረት በመጪው ወር የላይኛው ባሮአኮቦ፣ በመካከለኛው እና በታችኛው ስምጥ ሸለቆ፣ ኦሞጊቤ ተፋሰሶች እርጥበታማ ሁኔታ እንደሚያገኙ የሚጠበቅ ሲሆን፤ በጥቂት የላይኛው ተከዜ፣ መካከለኛው አባይ አዋሳኝ ከፍተኛ ቦታዎች፣ የላይኛው አዋሽ፣ የላይኛው ዋቢሸበሌና ገናሌዳዋ ተፋሰሶች ላይ መጠነኛ እርጥበት ሁኔታ እንደሚኖራቸው ይጠበቃል፡፡